


# « ህወሓት ከተሃድሶ የዝግጅት ምዕራፍ ወደማያቋርጥ የተግባር ምዕራፍ እየተሸጋገር ነው»

አቶ አለም ገብረዋህድ የህወሓት/ኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ አባልና የህወሓት ፅህፈት ቤት ኃላፊ

**የህወሓት/ኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ አባልና የህወሓት ፅህፈት ቤት ኃላፊየሆኑ አቶ አለም ገብረዋህድ ከወይን መጽሔት 41 ኛ ዓመት ቁጥር 54 እትም ጋር የህወሓት እና የትግራይ ሕዝብ የትጥቅ ትግል የጀመሩበትን የካቲት 11 ቀን 42 ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ ቃለ ምልልስ አድርገዋል። በዚህ ቃለ ምልልስ ከ1993 ዓ.ም ተሃድሶ ወዲህ ስለተገኙ ትሩፋቶችና ስለአጋጠሙ ፈተናዎች እንዲሁም አሁን እየተካሄደ ስላለው ጥልቅ ተሃድሶ ሂደትና ውጤት ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።እኛም ከመፅሄቱ የአገኘነው መረጃ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

ፍቃዱ ሞላ
በአዲስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የእለተ ሰንበት እትም አሰተባባሪ

## የ1993ዓ.ም ተሃድሶ

ከ15 ዓመታት በፊት የትግራይ ሕዝብ ሆነ በአጠቃላይ እንደ ሀገር ተሃድሶ ተካሂዷል። በተለይ የትግራይ ሕዝብ ከትጥቅ ትግሉ መጠናቀቅ በኋላ ወዴት፣ በምን እና እንዴት ብሎ ዳግም ወደ ሥልጣኔው የሚመለስበትና የሚታደስበት ሁኔታ አይቶ ነበር ማለት ይቻላል። በተሃድሶው መድረክ ሁለት ወሳኝ ድሎችን ተጎናፅፏል ማለት ይቻላል። አንዱ ድል የምንገነባው ሥርዓት ምንነት የሚመለከት ነው። ከተሃድሶ በፊት በምንገነባው ሥርዓት ዙሪያ ትልቅ ችግር ነበር። «ምን ዓይነት ሥርዓት እንዴት አድርገን እንገንባ? በሚገነባው ሥርዓት ሕዝብ እንዴት ተጠቃሚ ይሆናል? በሚለው ላይ ሰፊ የአመለካከት ድሪቶ የነበረበት ወቅት ነው።

ተሃድሶው የሚገባው ሥርዓት ምንነት፣ የሕዝብ ተጠቃሚነት በተመለከት በትግራይ ተጨባጭ ሁኔታ፣ በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች መሠረት ተደርጎ የጠራ መስመርና ሥርዓት የጥገኛና የድሪቶ አመለካከት ባለቤቶችን አሸንፎ በድል እንዲወጣ ያደረገ ነው። ስለዚህ መሠረታዊ ድሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ የትግራይ ሕዝብ ደግሞ በተለይ ከአስከፊ ድህነት፣ ድንቁርና ተመፅዋችነት ወጥተው በጥረታቸውና በትግላቸው በሥልጣኔ ማማ ላይ የደረሱ የዓለማችን ሕዝቦች ላይ መድረስ የሚያስችላቸው የጠራ መስመር ባለቤት መሆን ችለዋል።

ሌላው መሠረታዊ ድል ለሌሎች ድሎች ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግል ሊሰመርበት ይገባል። ይህ የጠራ መስመር መሠረት ተደርጎ የቀጣይ ድሎቻችን መሠረት የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች የዋናውንና የጠራውን መስመሩ ራእይ የሚያስተገብሩ ኢኮኖሚያዊ ፣ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ እድገት ለማምጣት ከየት ተነስቶ የት ይደርሳሉ የሚለው ከድሪቶ አስተሳሰብ ነፃ በሆነ አግባብ

የተመለሱበት ወቅት ነው። ስለዚህ ከደርግ ውድቀት በኋላ የተመሠረተው ሕዝባዊ መንግሥት ወይም ሕዝባዊ ሥርዓት ወደ ፈጣን የኅብረተሰብ ለውጥ እንዲቀየር መሠረት የተጣለበት ነበር ማለት ይቻላል።

ከተገለጸው ነገር ጋር የሚተሳሰር ቁልፍ ነገር ደግሞ የሥርዓቱ ምንነትና ባህርይ እንዲሁም ማስፈፀሚያ መስመር፣ ፖለሲዎችና ስትራቴጂዎችን ማጥራቱ ብቻ ሳይሆን የሚገነባው ሥርዓት በግንባታ ሂደቱ ላይ የሚያጋጥሙት ነገሮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የችግሩ አደጋ ምን ሊሆን ይችላል? በማለት በግልፅ ያስቀመጠ ነበር። የተለየው ቁልፍ አደጋ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለከካትና ተግባር የምንለው ነው። ይህ አደጋ ምድንነው?መነሻው ምንድን ነው? ባህሪው፣ መፍትሔውና አመካከቱ እንዴት ይሆናል? የሚል ሰፊና ዝርዝር ጥናት ተካሂዷል።

በተቻለ መጠን የዓለም ተሞክሮ በተለይ ደግሞ የሰሜን ምሥራቅ እስያ አገሮችን በመውሰድ የምንገነባው ሥርዓት የሚያጋጥመው ቁልፍ አደጋ፣ ባህሪውና አመካከቱ የመለሰ መስመር ነበር። ይህ ደግሞ በተሃድሶ ወቅት በጣም ልዩና ታሪካዊ የሚያደርገው ሁለተኛው ድል ነው። እነዚህ በተሃድሶ ወቅት የተመዘገቡ ወሳኝ ድሎች የኢትዮጵያን ሕዝብ የህዳሴ ጉዞ ያበሰሩና በ15 ዓመታት ውስጥ ለተመዘገበው አስደናቂ እድገት መሠረት ሆነው ያገለገሉ ድሎች ናቸው።

የ1993 ዓ.ም ተሃድሶ በተለይ በህወሓትና በትግራይ ሕዝብ ታሪክ በዓይነቱ ወደ ተለየ ምዕራፍ ያሸጋገረ ተሃድሶ ነበር ብለን መደምደም እንችላለን።

**የተሃድሶው ውጤቶች**

መስመሩ፣ ስትራቴጂዎቹንና ፖሊሲዎቹን ከ15ዓመታት በኋላ ሲፈተሹ በተግባር ተፈትነው በሁሉም መስክ ውጤት አስመዝግበዋል። ከአንድ ሺ ዓመታት የማያቋርጥ የቁልቁለት ጉዞ ላይ የነበረ ሕዝብና ሀገር በጠራው መስመር የቁልቁለት ጉዞው ተገትቶ ወደ ህዳሴ ጉዞ የሚወስዱ መሠረታዊ ድሎች መጨበጥ አስችሏል። ለመላው ሕዝብ፣ የህወሓት አባላትና ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታችን በድምር በመስመሩ ዙሪያ የማይጠፋ ችቦ ለኩሷል። የልማቱ ዋና ተዋናዮች አንድነት ፈጥረው በመንቀሳቀሳቸው ህወሓትና የትግራይ ሕዝብ እንደለመዱት በጋራ

እንዲሁም በፅናት በአደረጉት ጠንካራ ርብርብ አስደናቂ የሚባሉ ድሎች አስመዝ ግበዋል።

**ኢኮኖሚያዊ ልማት**

ተሃድሶው ካስመዘገባቸው ውጤቶች መካከል በኢኮኖሚው መስክ የተመዘገቡት ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህንም በገጠር እና በከተማ የተመዘገቡ በማለት በሁለት መክፈል ይቻላል።

**በገጠር**

በኢኮኖሚ ረገድ የትግራይ ግብርና ምን ላይ እንደነበርና በሌሎች ምን ይባል እንደነበር የሚታወቅ ነው። ብዙ ችግሮች ይነሳሉ፤ የትግራይ መሬት አፈሩ የተሸረሸረ፣የተፈጥሮ ሀብቱ የተመናመነ ነበር። ይህንን ለመቀልበስ በተቀመጠው ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የትግራይ አርሶ አደር መሬቱ፣ ውሃውና በማቀናጀት እንዲሁም በዋናነት የአርሶ አደሩ ለምግብ ፍጆታ ብቻ የማምረት አመለካከትና አስተሳሰብ እየተቀየረ በዓለም ገበያ ታሳቢ ያደረገ ምርታማነት ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ተችሏል። ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴንና የግብርና ግብዓቶችን በመጠቀም ምርታማነትን ማሻሻል ተችሏል። የምግብ ዋስትናም በማረጋገጥ ረገድ ድሎች ተመዝግበዋል።

ለውጡ በትልልቆቹ የኢኮኖሚ መለኪያዎች ሲመዘን ከድህነት ወለል በታች የነበረውን ሕዝብ ቁጥር ለመቀነስ ተችሏል። በትግራይ ከድህነት በወለል በታች የነበረው ሕዝብ ከ55 በመቶ የማያንስ ነበር። ባለፉት 15 ዓመታት በተደረገ ርብርብ ግን ወደ 22 በመቶ ማውረድ ተችሏል። ይህ ትልቅ ድል ነው። የሥራ አጥ ቁጥርም በገጠር ቀላል በማይባል ደረጃ ቀንሷል። በምርታማነት ረገድም ሲታይ የነፍስ ወከፍ ሄክታር ምርታማነት ከአምስትና ስድስት ኩንታል አይበልጥም። ባለፉት 15ዓመታት በተሰሩ ሥራዎች ግን በሄክታር ከ18 ኩንታል በላይ ምርት ማምረት ተችሏል። በአጠቃላይ ከተሃድሶ በፊት በትግራይ ይመረት የነበረው የግብርና ምርት ከ6ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል የማይበልጥ ነበር። በአለፉት 15 ዓመታት በተደረገ ርብርብ 18 ሚሊዮን ኩንታል የደረሰ ሲሆን፤ የመስኖ ልማት ሲደመርበት ደግሞ 30 ሚሊዮን ኩንታል ዓመታዊ ምርት የደረሰበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። ይህ መሠረታዊ ድል ነው። ስለዚህ የትግራይ

አርሶ አደር በከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ሥራዎች ታጅቦ መሬቱን እንዲያገግም ከማድረግ አልፎ በመስኖ፣ በእንስሳት ሀብት፣ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ ወተትና ስጋ የምርታማነት ለውጥ እያመጣ ይገኛል። በትግራይ ገጠር የሚኖር አርሶ አደር በሚያስገርም ሁኔታ ሀብት ማጠራቀም ጀምሯል። ከሺዎች አልፎ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ሀብት ያላቸው አርሶ አደሮች እየተፈጠሩ ነው።

በትግራይ ግብርና ላይ የተገኘው ለውጥ መሠረቱ ሲታይ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የተከተልነው ስትራቴጂ ተጠቃሽ ነው። የትግራይ ግብርና የተፈጥሮ ሀብት በመቀየርና በማሻሻል ላይ በተሰራው ሥራ የተገኘ ነው። በተለይ አፈሩ ከሚገባው በላይ የተሸረሸረ፣ ለዘመናት የተከላ፣ የአየር ጠባዩ የተዛባ፣ የተፈጥሮ ደን የመነመነ ነበር። በድርጅታችን የተፈጥሮ ሀብት ስትራቴጂ መሠረት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ በመስራት፣ ዘመናዊ የግብርና ግብአትና ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለውጥ በማምጣት ኢኮኖሚው ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር በሚያስችል ስትራቴጂ ተአምር ተሰርቷል ማለት ይቻላል።

በትግራይ ገጠር የመስኖ ልማትም ተካሂዷል። በእያንዳንዱ አርሶ አደር የውሃ ባንክ የመፍጠር ሥራ ተሰርቷል። ከገበያ ጋር የተሳሰረ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳት ሀብት ሥራ እየተስፋፋ ነው። የትግራይ አርሶ አደር ድርቅን የመመከት አቅሙ በሥነ ልቦና፣ በአደረጃጀትና በተጨባጭም ቁጠባ እያጠናከረ በመምጣቱ ጠንካራ ሆኗል። በአለፈው ዓመት አጋጥሞ የነበረው ድርቅን ሕዝብ፣ ድርጅትና መንግሥት መመከት መቻላቸው ማሳያ ነው።

በገጠር የተፈጥሮ ሀብትና የእርሻ ሥራን በአጠቃላይ ደግሞ ልማትን የሚያቀላጥፉ ታላላቅ መሠረተ ልማቶች ተሰርተዋል። በገጠር መሠረተ ልማት የሚታይ ለውጥ ማስመዝገብ ተችሏል። የገጠር መንገዶች በስፋት ተሰርተዋል። ከገጠር መንገድ ወደ አውራ ጎዳና የሚተሳሰሩ መንገዶችም ተገንብተዋል። ቀበሌዎችና ወረዳዎች የሚያስተሳስሩ መንገዶችም በስፋት ተሰርተዋል። የገጠር የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ቴሌ፣ የመጠጥ ውሃና የመስኖ ግድቦች የመሳሰሉ መሠረተ ልማቶችም ተሰርተዋል።

**በከተማ**

ከተሃድሶ በፊት በከተሞች በተወሰነ ደረጃ የተጀማመሩ የመሠረተ ልማት ሥራዎች የነበሩ ቢኖሩም በስፋት የከተማ መሠረተ ልማት ሥራ የተጀመረው ከተሃድሶ በኋላ ነው። ከተሃድሶ በኋላ በስፋት የተሰራበትና በስትራቴጂ በግልፅ የተቀመጠው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማስፋፋት ነው። ዘርፉ የተማረና ያልተማረ የከተማ ነዋሪ የሚያቅፍና ተጠቃሚ የሚያደርግ እንዲሁም ኢኮኖሚውን ማንቀሳቀስ የሚችል ነው። በአለፉት 15 ዓመታት በጣም ሰፊ የሚባል የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ተቋማት የማስፋፋት ሥራም ተካሂዷል። ሥራውን የሚያግዙ ሥልጠናዎች፣ የብድር አገልግሎት እንዲሁም ድጋፍና የገበያ ትስስር በስፋት ተሰርቷል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች ተጠቃሚም ሆነዋል።

በከተሞችም ልክ እንደ ገጠሩ ለውጥ መጥቷል። በከተሞችን በጥቃቅንና አነስተኛ ደረጃ የካፒታል እድገት መፍጠር ተችሏል። በዚህም ዝቅተኛ ገቢ ያለው የከተማ ነዋሪ ተጠቃሚ እየሆነ መጥቷል። ከቴክኒክና ሙያ የተመረቀው ወጣት በተለይ በጥቃቅንና አነስተኛ ሥራዎች እየገባ የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እየፈጠረ የመጣበት ድል ተመዝግቧል። መካከለኛና ከፍተኛ ኢንቨስትመንትም በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ መጥተዋል።

በአጠቃ]sይ ከተሃድሶ በኋላ በተፈጠሩ ማበረታቻ ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንት በስፋት መግባት ችለዋል። በዘመናዊ እርሻ፣ በኮንስትራክሽን፣ በገቢና ወጪ ንግድ፣ በማዕድን እንዲሁም ማኑፋክቸሪንግ ላይ የሚሳተፈው ባለሀብት ቁጥር እየጨመረ መጥቷል።

በትግራይ የኢንዱስትሪ ጉዞው በባለሀብቶች ብቻ ሳይሆን የትግራይ ሕዝብና ህወሓት በልዩ አጋጣሚ በአካሄዱት የትጥቅ ትግል ያገኙት ሀብት ከድል በኋላ በትግል ላይ የነበረው ሰው ተከፋፍሎት ከሚባክን «ሀብቱ ተሰብስቦ ትግራይን በማልማት ቢውል የተሻለ ነው» በሚል ደርጅት በከፍተኛ ኃላፊነት ወስኖ ያቋቋመው የትግራይ መልሶ ማቋቋም ተቋምም ጭምር ነው። ከኩሓ አነስተኛ የዱቄት ፋብሪካ በስተቀር ለፋብሪካ የሚሆን ማዕድንና የተፈጥሮ ሀብት የላትም ትባል የነበረችው ትግራይ የትግራይ መልሶ ማቋቋም ተቋም የኢንዱስትሪ መሠረት የሚሆኑ ፋብሪካዎች በመገንባት የትግራይ ሕዝብ የኢንዱስትሪ ባለቤት እንዲሆን የሚያስችል ታሪካዊ

ሥራ ሰርቷል።

የትግራይ መልሶ ማቋቋም ተቋም ከተሃድሶ በኋላ እየተጠናከረ መጥቷል። የትግራይ ሕዝብ የትላላቅ ፋብሪካዎች ባለቤት እንዲሆን፣ በሀገር ደረጃም በኢንዱስትሪና በፋብሪካ ዝቅተኛ እንዳይሆን የሚያስችል ሰፊ ኢንቨስትመንትና ኢንደስትራላ ይዜሽን አጠናክሮ ቀጥሏል። የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እና የባለሀብቶች አጋር በመሆን አልፎ በትግራይ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ የማይተካ ሚና እየተጫወተ የመጣ የትግራይ ሕዝብ ተቋም ነው።

የከተሞች ልማት ያለ መሠረተ ልማት የማይታሰብ ነው። በመንገዶች፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በመብራት፣ በባቡርና ውሃ ልማት የተለያዩ ግንባታዎች እየተካሄዱ ነው። በትግራይ ሆነ በኢትዮጵያ የመሠረተ ልማት ግንባታው በሚገርም ፍጥነትና ስፋት እየተካሄደ ነው።

ከመንገድ ጋር በተያያዘ በትጥቅ ትግሉ እንደ መገለጫ ነበር፤ ይኸውም የመጪዋን ትግራይ እድገት ለመግለፅ ቅስቀሳ ሲካሄድ መላው የትግራይ አርሶ አደር ከአእምሮው የማይረሳት የሚመስለኝ፤ ትግራይ በመንገድ የአልጋ ዓይን እናደርታለን» የሚል መፈክር ነበር። ይህ ከብዙ ሰዎች አእምሮ አይጠፋም። በተግባር አሁን ትግራይ በመንገድ «የአልጋ ዓይን» ሆናለች ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በሁሉም አቅጣጫ የተሳሰረ የመንገድ ፍሰት አለና።

በትግራይ የከተማነት መስፋፋት አለ። 30በመቶ የትግራይ ሕዝብ በከተማ መኖር ጀምሯል። በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ደግሞ 50በመቶ የትግራይ ሕዝብ ኑሮውን በከተሞች ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም ጤነኛ የከተሞች መስፋፋት መኖር አለበት። ከገጠር ለተሻለ ተጠቃሚነት ወደ ከተማ የሚፈልሰው በተለይ ከገጠር ለመማር የሚመጣው ወጣት በብዙ ምክንያቶች ወደ ገጠር ስለማይመለስ፣ ከፈጣን የኢንዱስትሪ እድገቱ ጋር ተያይዞ በግብርና ላይ የሚመጣው እድገት፣ ወደፊት ያለው የአግሮ ፕሮሰሲንግ ጋር አቀናጅተህ ሲታይ በቀጣይ በሚፈጠሩ ሰፋፊ የሥራ እድሎች የከተማ መስፋፋት የትግራይ ሕዝብ መለያ መሆኑ የማይቀር ነው። ስለሆነም በከተሞች ተጠቃሚነት ከገጠር ልማት ጋር ተጣጥሞና ተሳስሮ ወደ ከፍተኛ ልማት መሸጋገር የሚችል መሆኑን እያነን ነው።

በአጠቃላይ በኢኮኖሚ እየተመዝገቡ ያሉ ትላልቅ ለውጦችና ድሎች የቀደምት ሥልጣኔ ታሪክ ባለቤት የሆነው የትግራይ ሕዝብ ወደቀደመው ሥልጣኔው ለመመለስና ህዳሴውን ለማብሰር የሚያደርገው ተጋድሎ መሠረቶች ሆነው  በገጠርና በከተማ ኢኮኖሚያዊ እድገት መጥተዋል ብሎ ለመደምደም የሚያስችሉ ናቸው።

## ማህበራዊ ልማት

በማህበራዊ ልማትም ታላላቅ ድሎች አሉ።ትምህርትና ጤና ከትጥቅ ትግል በኋላ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውና የተሰራበት ነው።ከ1993ዓ.ም ተሃድሶ በኋላም ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በትምህርት ረገድ አንድ ህፃን በሶስት ኪሎሜትር ርቀት ውስጥ ከሃያና ሰላሳ ደቂቃ የማይበለጥ መንገድ ተጉዞ ትምህርት ቤት የሚያገኝበት ሁኔታ ተፈጥሯል።ለዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣የቴክኒክኒ ሙያና ኮሌጆች እንዲሁም ዩኒቨርስቲዎች በትግራይ እየተስፋፉ ነው።በአሁኑ ወቅት ባለ ዲግሪ፣ባለ ማስተርስና ፒ.ኤች.ዲ የሆነ የትግራይ አርሶ አደር ልጅ ቁጥሩ ቀላል አይደለም።

በጤና ረገድም ከተሃድሶ በኋላ መከላከልን መሰረት በአደረገው ፖሊሲ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።በተለይ ደግሞ የትግራይ ሴቶች በአመራርና በጤና ባለሙያዎች ታግዘው በሽታን ለመከላከል የለኮሱት የትግል ችቦ የእናቶችና የህፃናት ጤናን ማረጋገጥ ተችሏል።የእናቶችና ህፃናት ሞት ለመቀነስ በተካሄደ ማህበራዊ አብዮት ለውጥ ተገኝቷል።በወሊድ ግዜ የሚሞቱ እናቶችና ህፃናት ሞት መጠን በጣም ሰፊ በሆነ  ደረጃ መቀነስ ተችሏል።በጤና ጣቢያ የሚወልዱ እናቶች በአሁኑ ወቅት 72 በመቶ የደረሰበት ሁኔታ ተፈጥሯል።በጤና ዘርፍ የተለኮሰው የትግል ችቦ ድምር ውጤት ጉልበት ያለው ጤነኛ ህዝብ፣የተሻለ ጤንነት ያለውና በልማት ንቁ ተሳታፊ ህዝብ የመፍጠር፣በህይወት የመኖር የእድሜ ጣራ በአማካይ 64 ዓመት ማድረስ የሚያስችል ስራ ተሰርቷል።ስለዚህ በጤናው ዘርፍ የተመዘገበው ድል ወደፊት የጤና ስራዎች ትራንስፎርም ለማድረግ መሰረት የሚሆኑ ታላላቅ ፍጻሜዎች የተመዘገቡበት ነበር ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል።

## ፖለቲካዊ አስተዳደር

በፖለቲካ አስተደዳር ቁልፉ ጉዳይ ህገ መንግሰታዊ ስርዓት መገንባት ነው።ህገ መንግስት በሃገር ደረጃ የፀደቀው ከተሃድሶ በፊት ነው።ከተሃድሶ በፊት ከተመዘገቡት መሰረታዊ ድሎች ዋናው ነው።ይችን ሃገር ማረጋጋት የቻለ፣ጤነኛ አስተደዳር እንዲኖር ያስቻለ ህገ መንግስት ነው። ከተሃድሶ በኋላመ ይህን ህገ መንግስና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ተጠናክሮ ቀጥሏል።በዚህም ታላላቅ ድሎች ተመዝግበዋል።አብዛኞቹ የሃገራችን ምርጫዎች ከተሃድሶ በኋላ የተካሄዱ ናቸው።በዚች ሃገር የስልጣን ምንጩ መሳሪያ መሆኑ ቀርቶ የምርጫ ካርድ የስልጣን ምንጭ ሆኗል።

ከተሃድሶ በኋላ ተጠናክሮ የቀጠለው ድል ደግሞ ያልተማከለ ስርዓት፣በተለይ ሰፊው ህዝብ የሚተዳደርበት የአስተዳደር ደረጃ፣የስልጣን ከፍፍል ባልተማከለ ደረጃ ወደ ህዝብ እያወረድክ የመሄድ ስራ ከተሃድሶ በኋላ በስፋት የተሰራበት ነው ማለት ይቻላል።ስለዚህ ከተሃድሶ በኋላ በትልቁ የተሰራው ህዝቡን ባልተማከለ ስርዓት ስልጣንን ከፋፍሎ ወደ ህዝብ እንዲደረስና ሰፊው ህዝብ ተጠቃሚ እንዲሆንና እንዲለምደው የሚያድርግ ሰፊ እንቅስቃሴ ተካሂዷል።ታችኛው መዋቅር የህዝቡ ነው።የቀበሌና የወረዳ አደረጃጀቶች እንዲሰለጥንና እንዲበቁ የሚያስችሉ ስራዎችም ተሰርተዋል።

ከተሃድሶ በፊት ምክር ቤቶች የነበሩ ቢሆንም ህግ አስፈፃሚው፣ህግ አውጪውና ህግ ተርጓሚው ሁሉም ተደበላልቀው የሚሄዱበትና ህግ አስፈፃሚው ጎልቶና ጎልብቶ የታየበት አካሄድ በስፋት ይታይ ነበር።ከተሃድሶ በኋላ የነበረው መደበላላቅ በተለይ ደግሞ ህግ አውጪውና ህግ ፈፃሚው የነበረው ተደባልቆ መሄድ በማስወገድ ምክር ቤቶች ለህግ አስፈጻሚው የሚቆጣጠሩበት ህጋዊ ነፃነት፣ፖለቲካዊ ነፃነት ተረጋግጧል።የሚቀረው ነገር ቢኖርም ምክር ቤቶች ከግዜ ወደ ግዜ እየተጠናከሩ፣አደረጃጀታቸውና አሰራራቸው እየተሻሻለና እየተጠነከረ፣ህግ አስፈፃሚውና ህግ ተርጓሚው/ዳኙነት/ በመቆጣጠር ረገድ በምክር ቤቶች በኩል እየተጠናከረ የመጣበት ሁኔታ በስፋት ይታያል።

ከተሃድሶ በኋላ የህዝባችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ በልማት፣በአስተደዳር፣በእቅዶች አፈፃፀምና ተጠቃሚነት በስፋት እየተሳተፈና እየገመገመ በመሄድ ተጠናክረው የመጡ ሁኔታዎች እናያለን። የዴሞክራሲ ተቋማት አደረጃጀትና መልካም አስተደዳር ከተሃድሶ በኋላ እየተጠናከረ መጥቷል። የህግ የበላይነት ለማጠናከር የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል ሰፋ ያሉ ማሻሻያዎች ስራ ላይ ውለዋል።ስለዚህ በፖለቲካዊ አስተደዳር መስክ ህግ መንግስቱን መሰረት በማድረግ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመሰላቸው ሃሳብ ይዘው የሚታገሉበት፣ህወሓት/ኢህአዴግም ከተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በየግዜው የሃገሪቱን ፖለቲካዊ አስተዳደርና ተሳትፎ በሚያጠናከር መንገድ እየሰራ የመጣበት ሁኔታ አለ።

**የድርጅት አመራር አቅም**

በህብረሰተብ የለውጥ እንቅስቃሴ የአንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ድርጅት፣እንደ ህወሓት/ኢህአዴግ የመሰለ ተራማጅ ህዝባዊ ድርጅት፣ሃገርና ክልል ለመለወጥ በሚደረግ እንቅስቃሴ ለድውቀትም ለድልም መስመሩ ወሳኝ ነው።እንደኛ በመሰለ ህዝባዊና ተራማጅ ድርጅት ደግሞ ለድሉና ለብቃቱ ከሚወስኑ ዋናው ቁልፍ ነገር የጠራ መስመር ነው።

የጠራ መስመር በለለበት ማንኛውም ዓይነት ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት ቢኖርም ህዝብን መርተህ ወደ ድል ማድረስ አይቻልም።ህወሓት/አህአዴግ በተለይ ደግሞ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ በመሰረታዊ ይዘቱ ለትግራይ ህዝብ በአጠቃላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ገቢ ለማድረስ የሚያስችል መስመርና ስትራቴጂ አለን።ይህ በየግዜው ከሁኔታዎች ጋር የሚሻሻል የጠራ መስመር ባለቤቶች ነን።ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ከተሃድሶ በኋላ በዚህ መስመር ተጠናክረው ወጥተዋል።

አንዳንድ ሰው«ህወሓት ተዳክማለች»ብሎ የሚያስብ፣የሚጨነቅ አለ።መጨነቁ ጥሩ ነው፣ነገር ግን ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ለማጠናከር ከሁሉም በፊትና በላይ መመዘን ያለበት እንደ ህዝብ ለመለወጥና አንድ ደረጃ የኢኮኖሚ ለውጥና አኗኗር ለመሸጋገር የሚያስችለው መስመር ባለቤት የሆነ ህዝብ መሆን ነው።ይህ ህዝብና ድርጅት እስካሁን ድረስ ከአሰበው መድረስ የሚያስችለው

መንገድና ጉዞ ባለቤትና ድል የተቀዳጀ ህዝብና ድርጅት ነው።ስለዚህ የትግራይ ህዝብ ሆነ ህወሓት ህብረተሰብን መለወጥ የሚችል መስመር የጨበጠ፣አስደናቂ ድል በትጥቅ ትግል ጭምር ማስመዝገብ የሚያስችል የጠራ መስመር ያለው ነው።መስመሩን መሰረት አድርጎ የታገለ ነው። ሁሉም በመስመሩ ማሰባሰብ ያስቻለ ነው።አሁነም ሁሉንም ማሰባሰብ የሚያስችል፣ጥቅሙን ሳያጓድል ነቅቶ እንዲታገል ያደረገው የሚያጓጓ መስመር ባለቤት ነው።ወጣቱ፣ሴቷ፣ምሁሩ ሳይቀር በአጠቃላይ የገጠርና የከተማ ህዝብ በጠንካራ ዲስፕሊን የሚዋደቅለት፣አንዱ ቢቀር፣ አንዱ ቢወጣ፣አንዱም ቢኖር እነዚህ ሃይሎች በጠንካራ ዲስፕሊን  የሚዋደቁለት መስመር ባለቤት የሆነ ህዝብና ድርጅት ነው።

መስመሩን በመተግበርና በመስፈፀም ችግሮች ቢኖሩም፣ድክመቶች ቢኖሩም አሁን እንዳደረግነው ተሃድሶ  ዋናውን መስመር ይዘን፣እሱን ማሳያና መተንተኛ እያደረገን ችግሮች እየፈታንና በወቅቱ ሳይንሳዊ  በሆነ መንገድ እያየን መሄድ የሚያስችለን መሰረታዊ ትጥቅ የያዝን ህዝብና ድርጅት ነን።

**የድርጅቱ የድልና የለውጥ ምንጭ**

የድሉ እና የለውጡ ምንጬ የብቁ አብዮታዊ ዴሞክራት ድርጅት እና አመራር  ናቸው። የድርጅታችን ህወሓት ተነፃፃሪ ፖለቲካዊ ብቃትና ጥንካሬ ውጤቶች ናቸው።ፈተናዎችና ችግሮች በብቃት የማለፍ ልምድን ችሎታ ያለው ድርጅት፣ሁኔታዎችን የመረዳትና በሳይንሳዊ መነፅር የመፍታት አቅም ያለው ድርጀት  ውጤት ነው።ሳይንሳዊ በሆነው መስመሩ ችግሮቹን እየፈታ የመጣና እየገሰገሰ ያለ ደርጅትና ህወሓት የመራው ጉዞ ነው።እውነቱ ይኸው ነው።

ሌላው የትግራይ ህዝብ የጠራ መስመሩን ጨብጦ በመሰባሰብ በሚያስገርም መንገድ ልክ እንደ ትጥቅ ትግሉ ያስመዘገበው ውጤት ነው።እንደ ልማዱ ተደራጅቶ በአደረገው ከፍተኛ ትግል የመጣ ድል ነው።ዋናው ተዋናይ ህዝቡ ነው።

የትግራይ ህዝብ ትናንት በመራራው የትጥቅ ትግል በአስደናቂ ፅናት፣ጀግንነትና ድል አድራጊነት መንፈስ ያስመዘገበው ድል እንደገና ከተሃድሶ በኋላ ደግሞታል።የትጥቅ ትግል ልምዱን ከ1993

ዓ.ም ተሃድሶ በኋላም መጠነ ሰፊ በሆነ መንፈስ ትግሉን በተደራጀ መንገድ በማቀጣጠል ቁርጠኝነት በተሞላበት  እንደገና ቀጥሎበታል።

አሁንም ድርጅታችን ህወሓት ከ15ዓመታት በኋላ ቆም ብሎ እስከአሁን ያስመዘገባቸው ድሎች እንደ ልማዱ አጀንዳ ቀርፆ በተሃድሶ መልክ መላው ድርጅት፣መንግስትና ህዝብ የሚያዳረስ በጥልቀት የመታደስ ስራው አጠናክሮ እየቀጠለ ነው።ዛሬ ድርጅታችን ህዝባዊ አመለካከቱንና ተግባሩን የሚፃረሩ ጉድለቶችን አስወግዶ ህዝብን በከፍተኛ ደረጃ ለመምራት ከባህሪው ተነስቶ መስመሩ ላይ በፅናት ቆሞ እንደከዚህ ቀደሙ ወደ ፊት ለመወንጨፍ ተዘጋጅቷል።ህወሓትም ዛሬም እንደቀደመው በቦታው ላይ አለ።

**ጥልቅ ተሃድሶው**

የጥልቅ ተሃድሶው እንቅስቃሴ ሃገራዊ ነው።ሃገራዊው ተሃድሶ እንዴት መጣ የሚለው መጀመሪያ በትክክል ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው።ኢ.ህአዴግ እንደ አንድ ተራማጅ ድርጀት  ሁል ግዜ ውስጡን በየግዜው እየገመገመ የሚያይ ድርጅት ነው።

ህወሓት/ኢ.ህአዴግ አንዱ ዋናው መለያ ባህሪው ራሱን የማረም መሰረታዊ ባህርይ ያለው ድርጅት ነው።ከሌሎች ድርጅቶች የሚለየው መሰረታዊና ቁልፍ ባህሪው ይኸው ነው።ስለሆነም እንደ ህወሓት ይሁን እንደ ኢ.ህአዴግ ውስጡንና ሁኔታዎችን በተለይ ደግሞ ለመድረኩ የሚመጥን ብቃት ለማግኘት መድረኩን የሚመጥን አመለካከትና ጥራት እንዲኖረው ሁል ግዜ ውስጡን የሚገመግም ድርጅት ነው።ራሱን እየገመገመ በወቅቱ የሚያርም ድርጀት ነው።ይህን ባህሪው መሰረት አድርጎ ከሁለትና ሶስት ዓመታት በፊትም ግምገማዎች እያካሄደ ነበር።

ጥልቅ ተሃድሶ እየተካሄደ ያለው ዘንድሮ ነው።ከአጠቃላይ የስራዎች አፈፃፀም በመነሳት ችግሮችን መነሻ በማድረግ የድርጅት ሁኔታ፣የድርጅት አመራር  በመስመሩ እና በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መነፀር በማየት የግምግማ እንቅስቃሴዎች እያደረገ መጥቷል።የአሁኑ ተሃድሶ አንድ መሰረታዊ መነሻው ምንድነው?ካልን፤ ድርጅቱ ከባህሪው በሚመነጭ የሚታዩ ጉድለቶች ራሱን በራሱ ለማረም ነው።በቀጣይነትም ግምገማን እንደ አሰራር የሚጠቀም ድርጅት መሆኑ

መታወቅ አለበት።ህወሓት ሆነ ኢህአደግ እየገመገመ እያለም በሂደት በተፈጠሩ ጉድለቶችና ብልሽቶች ሰለባ የሆነ ህዝብ ጥቅሙን የሚፃረሩ ጉድለቶች እንዲታረሙለት እንቅስቃሴ እያደረገ መጥቷል።የህዝቡ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ነው።ህዝቡም ጥያቄዎቹን ሊመለሱለት የሚገባ መሆኑን፣ካልተመለሱለት ደግሞ ዝም ብሎ እንደማያይ በአደረጋቸው እንቅስቃሴዎች እያሳየ መጥቷል።

በእዚህ ሂደት ግን ትክክለኛ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ይዞ የተሰለፈ ህዝብና ይህንን እንደ መልካም አጋጣሚ ቆጥረው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቱን ለማፍረስ እንቅስቃሴውን የጠለፉ/የሰለቡ ጥገኛና ሃይሎችን ለየብቻቸው ለያይቶ ማየት ያስፈልጋል። እንደ ኢህአዴግ/ህወሓት በተፈጠሩ ችግሮች የተጎዳ፣ጥቅሙ የቀነሰበትና ያልተሟላለት ህብረተሰብ ከግዜ ወደ ግዜ ጫናውና ጥያቄው እየጨመረ መጥቷል።ስለዚህ ከህዝባችን የተነሳው ጥያቄና እንቅስቃሴ ፣ድርጅታችን ህወሓትም ሆነ ኢህአዴግ እየገመገሙት የመጡት ስለሆነ በአንድ ወቅት ሁለቱም ተገናኝተዋል።የህዝቡ ግፊትና በድርጅት ውስጥ የነበረው ግምገማ ተመሳሳይ ነው።ስለዚህ የህዝብ እንቅስቃሴና በድርጅት ውስጥ ይታሰብ የነበረና የተጀመረው ግምገማ ጎልብቶ እንዲወጣ አድርጎታል።

በሃገር ደረጃ የሚካሄደው እንቅስቃሴ መነሻው ምንድን ነው?ከተባለ ድርጅቱ በባህሪው ውስጡ እየገመገመ፣ራሱን ለማረም ያለው መሰረታዊ ባህርይና ፍላጎት፣የህዝቡ ደግሞ በድርጅትና በመንግስት የተፈጠሩ ጉድለቶች ሄደው ሄደው የህዝቡን ጥቅም የሚፃረሩ ስለነበሩ ጉድለቶችን አልሸከምም፣አልቀበልም፣አርሙ ብሎ የፈጠረው ተፅእኖና ጫና ሁለቱም ተደምረው የፈጠሩት ተሃድሶ ነው።ስለዚህ ከህዝቡ የመጣው ግፊት አስፈላጊና የተሃድሶ ድል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

የ1993ዓ.ም ተሃድሶ አንዱ መሰረታዊ ግቡ መስመሩ ሲፈፀም፣በድል ሲጓዝና ሲተገበር ህዝቡ ከመስመሩ ተጠቃሚ እየሆነ በሚሄደበት ወቅት ጥቅሙን የሚፃረሩ ጉድለቶች ምንም እንኳን ጥቃቅን ቢሆኑ ተቀብሎና ተሸክሞ የሚሄድ ህብረሰተብ እየተፈጠረ አይደለም።ሁለተኛ አንድ ነገር ከሰጠኸው በኋላ ቀጥሎ ከእሱ የሚመጣ ካልመለስክለት የማይተኛ ህዝብ ነው እየተፈጠረ

የሚሄደው የሚል ነው።ስለዚህ ምጋች ህዝብ መፍጠር የተሃድሶው ግብ ነበር።ኢህአዴግ/ህወሓት እንደ ድርጅት ሆነ መንግስት የፈፀሙት ጉድለት «አልቀበልም» ጥቅሞቹን የሚፃረሩ ጉድለቶች ናቸው ብሎ ወደ አደባባይም ወጥቶ ተቃውሞ ማሰማት መቻሉ የተሃድሶው ውድቀት ሳይሆን ድል ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነው።

የጥልቅ ተሃድሶው በሁለት ምዕራፍ ከፍሎ ማየት ይሻላል።አንደኛው በኢህአዴግ አራቱ ብሄራዊ ድርጅቶች በአሉበት እና አሁን ያሉት የድርጀቶቹ  አመራሮች በተሳተፉበት፣ከእነዚህ በተጨማሪ በድርጅቶቹ መተካካት መርህ የወጡ ነባር አመራሮች በተገኙበት የጋራ ሰፊ መድረክ ተካሂዷል።ይህ የጋራ መድረክ እንደ ኢህአዴግ በክረምት የተካሄደ ገንቢና ግምገማ ሂስ መልክ የነበረው ሰፊ መድረክ ነው።ይህ መድረክ እንደ ኢህአዴግ በጣም ግልፅነት፣ነፃነት የተሞላበትና የተሳታፊዎች ድፍረትም የታየበት መድረክ ነበር።በመድረኩ እንደ ኢህአዴግ የተሃድሶው መነሻ የሚሆን በቂ ሰነድም ተዘጋጅቷል።ግምገማውን በማጥለቅ የችግሮቹ ምንነት፣ይዘትና መልኩ፣ የችግሩ ፖለቲካዊ ትርጉምና አደጋው፣ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያለው ትርጉምና አደጋው፣የመፍትሄ አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ መግባባት የተደረሰባቸውና የተሃድሶው እለታዊ እንቅስቃሴው ሰነድ ሆኖ  የፀደቀበት ሰፊ መድረክ ነበር።ይህ ምዕራፍ እንደመነሻ በድል የተጠናቀቀ ነበር ማለት ይቻላል።

ሁለተኛው አስፈላጊው ምዕራፍ በኢህአዴግ ደረጃ የተቀመጡት መሰረታዊ የግምገማ መደምደሚያዎችና የፀደቁ ሰነዶች መነሻ በማድረግ ብሄራዊ ድርጅቶችም የየራሳቸው መነሻ ሰነድ አዘጋጁ።በየድርጅቶቹ አካባቢያቸውንና የድርጅቶቹ ሁኔታ የሚገልፅ የተሃድሶ ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ሰፊናና ጥልቅ ግምግማ፣ሂስና ግለሂስ ገብተዋል።በዚህ ሂደት ሁሉም እህት ድርጅቶች በስራ አስፈፃሚ፣በማእከላዊ ኮሚቴ፣የስራ አስፈፃሚ የማእከላይ ኮሚቴና የከፍተኛ አመራሩ የጋራ ግምግማና ሂስና ግለሂስ አካሂደዋል።የአመራሩ ግምገማ፣ሂስና ግለ ሂስ በመያዝ ደግሞ የአጠቃለይ ከፍተኛ አመራር፣የአጠቃለይ መካከለኛና ጀማሪ አመራር እንዲሁም ወደአጠቃላዩ የድርጀት አባል ሂደቱ ቀጥሏል።በዚህም ሰፊ የተሃድሶ መድረኮች አካሂደዋል።

በቀጣይም ወደ ህዝብ የማድረስ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ።

ህወሓት ጥልቅ ተሃድሶው ወደ ህዝብ አድርሶታል።በሁሉም የተሃድሶ መድረኮች የተለዩ የመታገያ አመለካከቶች በሁሉም ብሄራዊ ድርጅቶች ጥሩ በሚባል ደረጃ ተገምግሟል፣ሂስና ግለ ሂስ ተካሂዷል ብሎ መውሰድ ይቻላል።ሁሉም ብሄራዊ ድርጅት በግምገማው የለየው ጉድለት በሰፊው አይቷል።ስለዚህ በሁሉም ድርጅቶች የተካሄደው ተሃድሶ በድምር ሲታይ እንደ ኢህአዴግ ለትግል የሚመች፣በቀጣይ ወደ ጠንካራ የፀረ ድህነት ትግል ለመግባት የሚያስችል ትልቅ እድል ፈጥሯል ማለት ይቻላል።የአመለካከት ጥራት ለማረጋገጥ እድል የፈጠረ ነው፣ እያንዳንዱ ድርጅት ችግሮቹን ለመቅረፍና ህዝብን ለመምራት የሚያስቸለው ምቹ ሁኔታ የፈጠረ ተሃድሶ አካሂዷል የሚል ግምገማ ነው ያለው።

ድል የምንለው ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ እንጂ ትግሉ ገና ነው።ትግሉ ያለው ወደፊት ነው። ትምክህት፣ፀባብነት፣ፀረ ዴሞክራሲያዊነት፣ሙስና፣ብልሹ አሰራር...በአጠቃላይ የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉ ሂደት ነው፣አሰራር ነው።በዚህ ጥልቅ ተሃድሶ ተጀመረ እንጂ ያለቀ አይደለም። እስካሁን በአለው ትግል ግን ለቀጣይ ትግል መነሻ የሚሆን ትልቅ ድል ተመዝግቧል ብሎ መደምደም የሚቻል ይመስልኛል።

በጥልቅ ተሃድሶ የተለዩ ችግሮችና አደጋቸው

የ15 ዓመታ ጉዞ ስናይ ድሎች ብቻ የተመዘገቡበት ዓመታ ነበሩ ማለት አይቻልም። ከድሎች ጋር በየጊዜው እያደጉና እየተጠናከሩ የመጡ ጉድለቶችና ድክመቶችም ነበሩ። በድርጅት ውስጥ የታዩት ብልሽቶች ከድሎች ጎን ለጎን የመጡ ጉድለቶች ናቸው። ስለዚህ አሁን ያለንበት መድረክ በአንድ በኩል አስደሳች የሆኑ ድሎች የተመዘገቡበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድሎቹን የሚሸረሽሩ ምናልባትም ካልታገልናቸው ወደ ኋላ ሊመልሱን የሚችሉ ብልሽቶችና ችግሮች የታየበት መድረክ ነው ተብሎ መውሰድ ይችላል።

እነዚህ ብልሽቶችና ችግሮች ለድል ጉዟችን የፈጠሩት አደጋና ችግር ምንድን ነው? የሚለውን ለማየት እንሞክር። አንድ ከተፈጠሩት ችግር እንደ አደጋ ልናስቀምጠው የምንችለው እነዚህ ድሎች አሁን ከአሉበት በላይ ሊመዘገቡ ይችሉ ነበር። እነዚህ ብልሽቶችና ችግሮች በድርጅትና በመንግስት ቦታ እየያዙ፣ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ባይመጡ ኖሮ የተገለፁት መሰረታዊ ድሎች ከዚህ በላይ ሊሆኑና ሊስፋፉ ይችሉ ነበር። መሆን ካለበትና መሄድ በሚገባው መጠን አልሄድንም ስንል ዞሮ ዞሮ የመጀመሪያው የአድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ማየት እንችላለን።

የመጀመሪያው የአድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈፃፀም በእድገት የሄድንበት ርቀት አለ። በትራንስፎርሜሽን ግን በተፈለገው መንገድ አልሄድንም። ይህ የውስጥ ብልሽታችን ማሳያ ነው። ከዚህ አልፎ በግንባታ፣ በፈጠራ፣ የወጣቶችን የስራ እድልና ተጠቃሚነት በሚፈለገው መጠን አልሄድንም። ሌላ ብዙ ምሳሌ አንስቶ መግለፅ ይቻላል። ስለዚህ ለእኛ የፈጣን ልማት ጥያቄ የሞትና ሽረት ጉዳይ ነው። በውስጣችን የሚፈጠር እልቂትና መባላት እንዳይመጣ ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ቁልፍና መሰረታዊ ጉዳይ ነው። ብልሽቶቹ ደግሞ ፈጣን ልማቱን በመግታት ረገድ ትርጉም የነበራቸው ብልሽቶች ናቸው። ፈጣን ልማቱን በከፍተኛ ደረጃ መግታት ችለዋል።

እኛ ፈጣን ልማት እናምጣ ስንል ለመናገር ብቻ አይደለም። የበለፀጉት የምእራብ አገራት አሁን የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ 200ዓመታት ፈጅቶባቸዋል። እኛ ግን ረጅም አመታት በሚወስደው ልማት አይደለም እየሄድን ያለነው። ረጅም ዓመት የሚያስጉዝና የሚያስቆይ ሁኔታ የለንም።

እንደዚህ አይነት ረጅም ጉዞ ሊበትነን ካልሆነ በስተቀር አያድነንም። የእኛ ዋስትና ፈጣን ልማት ነው። ፈጣን ልማት ደግሞ የእነ ኮሪያ፣ ታይዋን፣ ቻይና የሚታይ ነው። ስለሆነም አርባና ሀምሳ ዓመታት ውስጥ የማረጋገጥና ፈጣን ልማት ለማምጣት ነው እየሰራን ያለነው። የዚህ አይነት ፈጣን ልማት መረጋገጥና የመልማቱ መጠን ገደብ የለውም። አቅማችን መፈፀም የሚችለውን ሁሉ መስራት ነው የሚያስፈልገው። ስለዚህ እኛ እነዚያ መሰረታዊ ድሎች የምንላቸው በደንብ ሊያዙ፣ ሊገለፁና ሊጣጣሙ ስላለባቸው እንጂ ድሎቹ በአጭር ጊዜ እንደርስበታለን ካልነው ጉዞ አንፃር ሲመዘኑ የሚያኩራሩ ድሎች አይደሉም። ምንያቱም ግባችን ከዚህ በላይ እየሄድን አርባና ሀምሳ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ህዝባችን እንደ አደጉት ሀገራት ህዝብ ከፍተኛ ገቢ ላይ እንዲደርስ ስለሆነ ነው። ጉዞአችንና እምነታችን በእንደዚህ አይነት ሀይልና አስደናቂ የልማት ፍጥነትና ጉዞ መሄድ ነው።

አስደናቂ ደል አስመዝግበናል ነገር ግን እነዚህ ድሎች በአርባና ሀምሳ ዓመት ለመድረስ ካሰብነው ጋር ስታዩ የሚያኩራሩን አይደሉም። እንደ ድርጅት ሆነ ህዝብ በእነዚህ ድሎች የምንረካ አይደለንም። ስለዚህ ጉድለቶቻችን ይህንን የመሰለ ተአምራዊ ልማት በአጭር ግዜ እንዲረጋገጥ የሚያስችለው ወኔውን ይዞ እንዳይሄድ የሚያደርጉ ብልሽቶች መሆናቸውን አይተናል።ለፈጣን ልማት እንቅፋ መሆናቸውንም በግምገማችን ለይተናል። ብልሽቶች በልማታችን ላይ ተጨባጭ አደጋና እንቅፋት ፈጥረዋል። ፈጣን ልማት ለማስመዝገብ የመምራት ብቃታችን የሚያመክኑ፣ መስመሩን የማስፈፀም ችሎታችን የሚሸረሽሩ፣ በዋናነት የአመራሩና የመፈፀም አቅም የፈተኑ ችግሮችና ብልሽቶች ናቸው። በዚህ ምክንያት የልማት፣የመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ስራዎቻችን መሆን በአለባቸው መጠን እንዳይጓዙ፣ እንዳይቀጥሉ፣ አንቅፋት የሆኑ ተጨባጭ ብልሽቶች ናቸው ብለን ወስደናቸዋል።

ሌላው ፈተና የገለፅናቸው ድሎች ለህዳሴ ጉዞአችን መሰረታዊ ድሎች ናቸው። ነገር ግን እነዚህ አስደናቂና አስገራሚ ድሎች ጅምር ላይ ያሉ ናቸው። እነዚህ ድሎች ተጠራቅመው ህዝቦች መድረስ ካለባቸው የዕድገት ደረጃ ማለትም መጀመሪያ፣ ታችኛው መካከለኛ ገቢ፣ቀጥሎ ከፍተኛ

መካከለኛ ገቢ፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ ከፍተኛ ገቢ የሚባሉት ደረጃዎች አንፃር ሲመዘኑ እነዚህ ድሎች ተደምረው ወደ ታችኛው መካከለኛ ገቢ እንደ ህዝብ ሆነ እንደ ሀገር አልገባንም። ይህንን ድል አላረጋገጥንም። ይህ ገና 2017ዓ.ም ላይ ነው የምናረጋግጠው። ስለዚህ ሁሉም ድሎቻችን ተደምረው ገና ወደዚህ ገረጃ አልተሸጋገርንም።

ስለሆነም በፍጥነት ወደ ታችኛው መካከለኛ ገቢ ለመድረስ የሚደረገው ርብርብ በጊዜ የለም ሂሳብ በተሸነሸነ የጊዜ ሰሌዳ ለመድረስ እልመን እየሄድንበት ያለነው ነው። እነዚህ ብልሽቶች ግን ይህን ጉዞ በፍጥነት ሂዶ ወደ ድል እንዳይደርስ በማድረግ ረገድ አሉታዊ ሚና ያላቸው ናቸው። ብልሽቶቹ በአግባቡ ካልታገልናቸው የመቆም ወይም ወደ ኋላ የሚመልሱን ፈተናዎችም ሊሆኑ ይችላሉ።

በጅማሬ ያሉና ወደ አንድ ጠንካራ መሰረት ያልተሸጋገሩ ድሎችን በመቅላት፣ በማጨናገፍ በሌላ አገላለፅ ድሎቹ ወደ ፊት የመገስገስ ፍጥነታቸውን በመግታትና በማኮላሸት የህዝብ ፍላጎትና የልማት ጉዞን እንዳይመጣጠን በማድረግ በህዝቡ ውስጥ ተስፋ የመቁረጥ አመለካከት በመፍጠር ወደ ሁከትና ብጥብጥ ማምራት የሚያስችሉ ችግሮች ናቸው። ይህ ንድፈ ሀሳብ አይደለም። **በተግባር ፈጣን ልማትና መልካም አስተዳደር ህዝብ በሚፈልገው መጠን አለማረጋገጥና አለመቀጠል መኖሩን ህዝብ አይቶ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ያሳየው ተቃውሞና ሁከት የእዚህ ምልክት ነው። እሱ በፈለጋት መጠን ልማትን ማምጣት** ካልቻልክ ምን ሊፈጠር እንደሚችል በተግባር አይተናል። እዚህም እዚያም አንድ አይነት ጥቅምና አሰላለፍ ያላቸው ህዝቦች በትምክህትና ጠባብነት አመለካከት ተሰልበው እርስበርስ ለመጋጨት ሞክረው ነበር። የእነሱ ባልሆነ ጥገኛ አመለካከት ተጠልፈው ህዝቦች እርስ በእርስ ለመገዳደል ሞክረዋል። ስለዚህ በውስጣችን የተፈጠረው ብልሽት ህዝቦች እርስ በእርስ ሊበላሉ የሚያደርስ ነው።ሀገር እንድትበተን የሚያደርግ ምልክት ነው ያየነው። ስለዚህ የገመገምነው ብልሽት ይህን ያህል መሰረታዊ ትርጉም አለው።

እነዚህ ብልሽቶችና ችግሮች በወቅቱ ካልታገልናቸው ድልና ብልሽት አብሮ አይሄድም። ወይ

ድሉ በአስተማማኝ መሰረት ላይ ሆኖ ብልሽቶቹ እየተቀበሩ ትርጉም ወደማይኖራቸው ደረጃ እየወረዱ ድሉ እያበበ ይሄዳል፤ወይ ደግሞ ድሉ ገገር መሆኑ እየቀረ ውስጣዊ ብልሽት የበላይ ሆኖ ቦታ እየያዘ የሚመጣበት ሁኔታ ይፈጠራል። ብልሽቱ የበላይ እየሆነ ከሄደ ድሎቻችን ስለሚሸረሽሩ ከድህነት አዙሪት የመውጣትና ታችኛው መካከለኛ ገቢ ለመድረስ ያልምነው ግብ አይሳካም። ስለዚህ ችግሮቹን ካልታገልናቸው በድህነት አዘቅት ውስጥ እንድንኖር ያደርጉናል።

በ1950ዎቹ አካባቢ ብዙ ሀገሮች መንግስታትና ህዝቦች ከድህነት ለመውጣት ጥረት ያደርጉ ነበር። ነገር ግን በሂደት አሁን በገልፅኳቸው መሰረታዊ ብልሽት ሲዘፈቁ ግን መውጣት አቅቷቸው፣ በድህነት አዘቅት ውስጥ ገብተው በመበታተንና በአለመረጋጋት ደረጃ የደረሱ የአፍሪካና የአለም ሀገራት ብዙ ናቸው። ወደኛ ሀገር ሁኔታ ስናይ ያየነው ምልክት ተመሳሳይ ነው። እንዲህ አይነት ሁከትና ብጥብጥ መፈጠር የፀረ ድህነት ትግላችን እየተንከባለ ፣ግዜ እየወሰደ መሆኑ ነው። ከዚህ በፍጥነት መውጣት ካቻልን በችግሩ ተዘፍቀን መውጣት አቅቶን እንድንኖር ያደርጋል። እነዚህ ብልሽቶች አደጋ የሚፈጥሩ ናቸው።

በሀገራችን ሁኔታ የድህነትን ማነቆ በጥሰን መውጣት ካቻልን ከድህነት ጋር ተስማምተን መኖር አንችልም። ከድህነት ጋር ተስማምተን የምንኖርበት ታሪክ አብቅቷል። የሚያስከትለው አደጋ እልቂትና መበታተን ነው። እንደኛ ባለ ቡዝሀነት ባለበት ማህበረሰብ ትምክህትና ጠባብነት በሰፊው የሚታዩበትና ህዝብ ከህዝብ ጋር በዘር የሚጨፋጨፍበት እድል ባለው ህብረተሰብ ውስጥ ድህነትን ይዞ መጓዝ አይቻልም። አማራጩ ከድህነት መውጣት ነው። ከብልሽት መውጣት ነው።ችግሮቹ ትርጉም ወደማይኖራቸው ደረጃ ማውረድ ነው።

ድህነትና የውስጠ ድርጅት ብልሽት ትርጉም ወደማይኖራቸው ደረጃ ካልወረዱ ህወሓትም ይሁን ኢህአዴግ አደጋው እያንዣበበ ቆይቶ መጨረሻው እልቂትና መበታተን እንደሚያስከትል ይገነዘባሉ። እንዲህ አይነት ሁኔታ ከተፈጠረ ለዚህ ትውልድ የከፋ ውርደት ነው። ይህ የሚመጣው ደግሞ መስራትና መፈጸም ሳይቻል ሲቀር ነው። እንደ ድርጅትም መፍታት ካልተቻለ አደጋው ጥፋት ነው የሚለውን መነሻ በማድረግ በግምገማችን አይተነዋል።

**በህወሓት ተሃድሶ የተለዩ አደጋዎችና አስተሳሰቦች**

የጠባብነት፣ከባቢያዊነት፣ኪራይ ሰብሳቢነት ፣ ስልጣንን አላግባብ መጠቀምና ሌሎችንም ችግሮች አንድ በአንድ አይተናቸዋል። እያንዳንዳቸው ባህሪያቸውና መነሻቸው ተንትነን ገምግመናል። ሂስና ግለ ሂስ አካሂደናል። መሰረታዊ ትርጉማቸውን አይተናል። ከላይ እስከ ታች ተራ አባሉና አመራሩ በዚህ ሂደት እንዲያልፍ አድርገናል። አብዛኞቹ ችግሮቹ ያጠፉናል የሚል የጋራ መግባት ላይ ደርሰናል። ሁሉም ከችግሮቹ መውጣት አለብን ብለው ራሳቸውን ሂስ አድርገዋል። በችግሮች ዙሪያ የማያቋርጥ አብዮታዊ ትግል ተደርጓል። እስካሁን የተደረገው ተሃድሶ የዝግጅት ምዕራፍ ነው። በዝግጅት ምዕራፍ መነጽር ሲታይ የተሳካ ነበር። ችግሮቹ የሚያጠፉት መሆኑን ተገንዝቧል። ሊታገላቸውና ሊያስወግዳቸው እንደሚገባ ተረድቷል። በቀጣይ ሰፊ ትግልን ይጠይቃል።

ችግሮቹን እያቃለልልን ልማት መምጣት አለብን፣ መልካም አስተዳደር ማረጋገጥ አለብን፣ ችግሮቹ እንቅፋት ሆነውብናል፣ለህዝባችን ተገቢውን አገልግሎት አልሰጠንም ብለን ሂስና ግለ ሂስ አድርገናል። ነገ ደግሞ ህዝቡን ለማገልገል ወደ እሱ እንሄዳለን። ችግሮቹ ከነብስ ወከፍ የልማት ተግባራትና ፣መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ እየተዋሃዱ የማየቋርጥ ትግል እየተደረገባቸው የሚሄዱና የሚወገዱ ናቸው። ለእዚህም ነው **ህወሓት ከተሃድሶ የዝግጅት ምዕራፍ ወደማያቋርጥ የተሃድሶ የተግባር ምዕራፍ እየተሸጋገር ነው** የምንለው። ከዚህ በኋላ ትልቁ ትግል ወደ ፊት ያለው ነው። በአንድ በኩል መታገል የሚያስችለን ምቹ ሁኔታ ፈጥረናል። በሌላ በኩል ደግሞ ለሰፊው ህዝብ ልማት ለማምጣት ፣መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ ለማረጋገጥ በምናደርገው ርብርብ ነው የምንፈተነው። በዚህ ሂደት የተሻለ የሄዱ አመራሮችና ሲቪል ሰርቫንቶች እናንተ ጥሩ ሄዳችኋል ይባላሉ። ጥሩ ያልሄዱትም እየተነገራቸው ቀጣይነት ባለው ግንባታ፣ ግምገማ፣ ሂስና ግለ ሂስ ሂደት እያበቃን ህዝቡን የማገልገል አጠቃላይ አመለካከት እያጠናከርን ብልሽቶችን ማስወገድ እንችላለን።

**ፖለቲካዊና ህጋዊ ተጠያቂነት ከ1993 ተሃድሶ አንጻር**

የ1993 ተሃድሶ መሰረታዊ ባህሪው መስመርን ማጥራት ነው። መስመሩን ማጥራት ማለት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጎልብቶ እንዲወጣ እሱ ላይ የነበሩ መደናገሮችና ድሪቶ አመለካከቶችን ማስወገድ ነው። ጥገኛና የመበስበሰ አደጋ በአንድ በኩል  አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር በሌላ ሆነው ከፍተኛ ትግል የታየበትና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር አሸንፎ በድል የወጣበት ነው። የጥገኛ የመበስበስ ሀይል የተገለለበት ሁኔታም ተፈጥሯል። የዚህ ወኪል የሆኑ አመራሮች ሆነ ግለሰቦችም ከድርጅቱ ተሰናብተዋል። በፖለቲካዊ ትግል ከዚህ በላይ ተጠያቂነት የለም። በፖለቲካዊ ትግል  በድርጅት ውስጥ ጥገኛ አስተሳሰብን በግልም ሆነ በቡድን በመወከልህ ተጠያቂ ሆነህ ከመሰናበት በላይ ተጠያቂነት የለም። የ1993ዓ.ም ተሃድሶ ከፖለቲካዊ ተጠያቂነት በተጨማሪ በቂ መረጃ የተገኘበት በህግና በአስተዳደር መንገድ እንዲጠየቅ አስችሏል።

<u>ከ15 አመታት በኋላ እያካሄድን ያለነው ተሃድሶስ?</u> ተሀድሶ ሲባል ድርጅት አጀንዳ ቀርጾ የሚያቀጣጥለው እንቅስቃሴ ነው። ቆም ብለን አጀንዳ ቀርጸን የምናካሂደው ሰፊ የተሃድሶ እንቅስቃሴ አለ። አሁን ያደረገው ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቆም ብለን ውስጣችን ለመገምገም ያካሄድነው የተሃድሶ እንቅሴቃሴ  የመስመር ማጥራት አይደለም። የጠራ መስመር አለን። የርዕይ ማጥራት አይደለም። የጠራ ርዕይ አለን።  የአሁኑ የተሃድሶ እንቅሴቃሴ በተግባር ተፈትኖ አስደናቂ ድሎችን እያስመዘገበ ያለን  መስመርና ርዕይ በማስፈጸም ረገድ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከት ውጭ እየተፈጠሩ ያሉ ጥገኛና የመበስበስ ዝንባሌዎችና አመለካከቶች የመታገል ተልዕኮ የያዘ ነው። ማዕከሉ አብዮታዊ ዴመክራሲ ያልሆኑ  አመለካከቶችና ተግባራት መታገል ነው። አብዮታዊ ዴሞክራሲን መስመር የሚጻረሩ ያልጠሩ ችግሮች በርከት ባለ የድርጅቱ አባላት ላይ ሲታዩ እንዲሁም መስመሩና ርዕዩን የሚጻረሩ ያልጠሩ አመለካከቶችና ተግባራት ሲፈጠሩ ነው ተሃድሶ የሚቀጣጠለውና የሚካሄደው።

. የዚህ ዓይነት ተሃድሶ ባህሪው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ቁልፍ ችግር የአመለካከት ጥራት ችግር ነው፡፡ ያልጠራ አመለካከት የሚወስናቸው የተለያዩ የብልሽት ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህ

ተከትለው የሚመጡ ችግሮችም አሉ፡፡ በርካት የድርጅት አካል በአልጠራ አመለካከት ቁልፍ የሚባለው አብዛኛውን አካል ካልጠሩት አመለካከቶች ማዳን ነው፡፡ ማውጣት ነው፡፡ ወደ አንድ ግንባር እንዲመጣና እሱን መሰብሰብ ነው መሰረታዊ ስራ፡፡ በዚህ ምክንያት ነው መሰረታዊ የጥልቅ ተሃድሶ አመለካከት የማጥራትና የማብቃት ተሃድሶ ተብሎ የተሰራው፡፤ ዋናው ቁም ነገር ያልጠራውን አመለካከት ደግሞ በመመለስ(በማስተካከል) አብዛኛው አባል መሰብሰብ ዋና አላማው ነው፡፡ በዚህ ወቅት ተጠያቂነትና ከሰው ጋር ማገናኘት የሚባለው እያንዳንዱ ሰው ሂደት ሂስ የሚያደርግበት፣ ተሳስቼ ነው ብሎ ጉድለቱን የሚያነሳበት የፈጠረው ጉድለት በግሉ የድርሻውን የሚወስድበትና ተጠያቂ የሚያደርግበት የትግል አግባብ ተፈጽሟል፡፡ ችግሩ ሁላችንም ዘንድ አለ፡፡ የሁላችንም ሲደመር ትልቅ ችግር ይሆናል፡፡ ችግሩ ደግሞ በግላችን ነው የወሰድነው፡፡

እያንዳንዱ ሰው ተገምግሟል፡፡ ሂስ ተደርጓል፡፡ ይህ ማለት እያንዳንዱ ሰው በተጠያቂነት አሰራር አልፏል ማለት ነው፡፡ ተጠያቂነት ማለት ሰው ማሰር አይደለም፡፡ ሰው ወደ ማረሚያ ቤት መላክ ማለት አይደለም፡፡ ትልቁ ተጠያቂነት ሰው በሰራው ጥፋት ይጠየቃል፡፡ ይህ ዓይነት ጥፋት፣እንዲህ ዓይነት ችግር ፈጥሪያለሁ ብሎ እኔ ተጠያቂ ነኝ ብሎ ራሱን ሂስ እንዲያደርግ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ይህ ነው መሰረታዊ ስራ፡፡ ህወሓት ደግሞ ይህንን አድርጓል፡፡

እያንዳንዱ አመራርና አባል እስከ ህዝብ ድረስ ወርዶ ለተፈጠረው ችግር የእኔ ድርሻ ነው ስለዚህ ተጠያቂ ነች ብሏል፡፡ በዚህ የመጣ ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ ብሏል፡፡ ሁሉም በዚች ጉድለት ተጠያቂ ነኝ ብሎ የድርሻውን ወስዷል፡፡ ተጠያቂነት ማለት ይህ ነው፡፡ ተጠያቂነት ማለት ይህን ያህል ሰርቋልና ወደ ህግ አቅርበህ ማውረድ ብቻ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ ትልቁ ተጠያቂነት እያንዳንዱ ተሳስቼ ነበር ህዝቤና ድርጅቴን ለመካስ ዕድል ይሰጠኝ ማለቱ ነው ተጠያቂነት ማለት፡፡ እያንዳንዱ ሰው በዚህ ችግር ምክንያት ልማትና መልካም አስተዳደር እንዳይነግስ ህዝቦች በድዬ ነበርና ለመካስ ዕድል ይሰጠኝ፣በዚህ የመጣ ከሆነ ቅጣት ተጠያቂው እኔ ነኝ ብሎ ታድሷል፡፡

ተሃድሶው አላማ አብዛኛው በዚህ አይነት የተጠያቂነት መንፈስ ወደ አዲስና የተሟሟቀ ትግል ማሳገባት እንጂ ማባረር አይደለም፡፡ በተፈጠረና በሚመጣ የአመለካከት ለውጥ እድገትና ፍጥነቱ የሚለካ የተሃድሶ መድረክ ነው፡፡ ሲጀመር እዚህ ያለው የተሃድሶ አስተሳሰብ መስተካከል አለበት እላለሁ፡፡ የችግሮቹ ሁሉ መሰረት የሙስናና ብልሹ አሰራር ጨምሮ ጥገኛና የመበስበስ ዝንባሌ ነው፡፡ የሙስና መሰረቱ ደግሞ ሥልጣን ለህዝብ ሳይሆን የመኖሪያ እና የግል ምቾት ምንጭ አድርጎ የማየት ዝንባሌ ነው።ይህን ሁሉን ነገር የፈጠረው፡፡ ብልሹ አሰራር እንዲኖር ሙስና እንዲተገበር መሰረቱ የዚህ ዓይነት አመለካከት ነው፡፡በተሃድሶ እንቅስቃሴ የተለኮሰው የዚህ ዓይነት ችግሮች ከመሰረቱ የሚያደርቅ የብልሹ አሰራርና የሙስና መሰረት የሆነው አመለካከት ለመቅበር የሚያስችል ትግል ነው ፡፡ በዚህ መነጽር ሲታይ የተሃድሶው ትግል የተሳካ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን በጣም የተበላሸውን ከመስመር የወጣውና የበሰበሰው ከአመራር እስከ አባል ደረስ አስተማሪ በሆነ መንገድ እርምጃ ተወስዷል፡፡ የማባረር፣ የማሽጋሸግ እርምጃም ተወሳዷል፡፡

ምናልባት አንዳንድ ሰው የማእከላዊ ኮሚቴና ስራ አስፈፃሚ ካልተሽጋሸጉ እርምጃ አልተወሰደም ብሎ የሚያስብ፣ምናልባትም ችግሮች ቀርበው እያለ በይሉኝታና በመሸማገል እርምጃ መውሰዱን ትትውት ይሆን ይሆናል የሚል ጥርጣሬ የሚያነሳ ሰው ይኖራል።የተወሰነው ግን እንዲህ የሚለው ከተቆርቋሪነት መንፈስ አይደለም።አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደ ሃይል፣አመለካከትና መስመር እንዲጠናከር ፍላጎት የለለው ነው።የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመራር እንዲፈረስ ፍላጎት ስላለው ነው።የሆኖ ሆኖ በህወሓት የባሰ ችግር በአለባቸው ሰዎች ላይ መወሰድ ያለበት እርምጃ ተወስዷል።መሽጋሸግ ያለበት ተሽጋሽጓል።ከአመራር ሳይቀር ወደ ህግ የቀረቡም አሉ።በሌላ በኩም ሽግሽግ ሲባል ሂስ አድርገህ ማባረር ብቻ አይደለም።በአቅምና በተዛማጅ ችግር ህዝቡን ማገልገል የማይችል አመራር ወደሚመጥነውና ህዝበን ማገልገል ወደሚችልበት ደረጃ በአደረጃጃት ምድባ የተስተካከለ አለ።ስለዚህ የተሃድሶው መሰረታዊ አሰራር ትግልና የአመለከካት ጥራት ነው።የተሳሳተ አመራርና አባል ገምግመህ ከጉድለቱ ነፃ በማውጣት የሚታገልበት መንፈስ

መፍጠር ነው የተሃድሶው መሰረታዊ ግብ ነው።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ነገር አለ።በግል በህግ ተጠያቂነት የሚያስከትል የሙስና ተግባር ከተገኘ በህግና በአስተዳደራዊ ጉዳይ የሚጠየቅ መሆኑ መጠራጠር አይገባም።ነገር ግን እንዲህ ዓይነት የሙስና ችግር በግምገማ፣ በሂስና ግለሂስ ቁልጭ ብሎ ይዋጣል ተብሎ ነው የሚጠበቀው? ስራ አስፈፃሚው ሆነ ማእከላዊ ኮሚቴው በአንክሮ አይቶታል።ምክንያቱ የሙስና ወንጀል የተወሳሰበ ነው።በግምገማ ፣ ሂስና ግለሂስ የመገኘት እድሉ ጠባብ ነው።የተወሳሳበ አፈፃፀም ነው ያለው።በቀላሉ ይገኛል ብሎ መውሰድ አይቻልም። ስለዚህ በማእከላዊ ኮሚቴ ይሁን በስራ አስፈፃሚ በቀጣይ በሌሎች የመቆጣጠሪያ አሰራሮችና አደረጃጀቶች በማጠናከር በቀጣይ ትግል እንዲታይ መግባባት ላይ ተደረሰ እንጂ የለም ተብሎ የተዘጋ ፋይል አይደለም።

አሁን የሚታየው የሙስና ፖለቲካዊ መሰረቱ ነው።ይህም የአመለካከት ችግር ነው።ይህ ደግሞ ትግል ተደርጎበታል።ሙስና የለም ከሙስና የፀዳን ነን ብሎ ህወሓት አላወጀም።መሄድ ያለብኝ ሄጃለሁ።ሙስና የራሱ ባህርያት መሰረት አድርጌ በቀጣይ እታገለዋለሁ ብሎ ነው ያስቀመጠው። በፌስቡክና በወሬ ደረጃ የሚባሉ ሁሉ ቀርበው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።ከዚህ በላይ መረጃ ይዘህ መታየት ያለበት ለማየት በሩ ክፍት ነው።ትግሉ ተጀመረ እንጂ አላለቀም።

ስለዚህ በአንድ በኩል ጤነኛው ሃይል አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ድርጅታችን እንዲጠናከር የሚፈልግ በዚህ መንገድ ሄደውበትን ይሆን ብሎ ለሚጠራጠር የተሰማችው የተወራችው ሁሉ ቀርባ ማብራሪያ ተሰጥቶባታል።ከዚህ በላይ መሄድ ያልቻልንበት ነገር ካለም ተደብቆ የሚቀር አይደለም እየታየ ይሄዳል።ይህን ህዝባችንና አባላችን ሊረዳው ይገባል።ይህንን ያላደረግን መስሎት ጥርጣሬ የገባው ካለ ይህንን አድርገናል።ስለዚህ በሆነው ባልሆነው እየተጠራጠርን መሄድ የለብንም።ማድረግ ያለብን አድርገናን የቀረ ካለም በቀጣይ ትግል ይካሄድበታል።አሁን ግልፅነት የተፈጠረ ይመስለኛል።በሃሜት የነበረው ሁሉ በግልፅ ቀርቧል።በግሌ እንደ አንድ የተሃድሶ ውጤት አድርጌ የሚቆጥረው በአመራሩ መካከል የተፈጠረው ግልፅነትና መግባባት

ነው።

**የመጠራጠር መንስኤው...**

ይህን በሁለት መንገድ ነው የማየው።የህዝብና የአባሉ መጠራጠር መሰረቱ ድርጅትን የማስተካከል ነው።የቀረ እና ያልታየ ነገር እንዳይኖርና ድርጅት ተጠናክራ ሳትወጣ እንዳትቀር ከማሰብ የሚመነጭ በመሆኑ ጤነኛና የሚደገፍ አመለካከት ነው።ሙሉ በሙሉ የታደሰ ህወሓት ለማየት ከመፈለግ የሚመነጭ ነው።ይህ ጤነኛ አመለካከት ስለሆነ መቀጠል አለበት።

በሌላ በኩል ጥቂት የተደራጁና ያልተደራጁ በቡድንና በግል ፀረ ወያነ የሆነ ጥገኛ ሃይሎች ግን ፍላጎታቸው ህወሓትን ማፍረስ ነው።አብዮታዊ ዴሞክራሲ ጠንክሮ እንዳይወጣ የሚፈልጉ ናቸው።ስለዚህ «ህወሓት አልታደሰም» የሚል መፈክር በየማህበራዊ ሚድያው ያስተጋባሉ። አላማቸው ያልጠራ መዋቅር ስላለ እሱ የጠራ እንዲሆን ሳይሆን እርምጃ አልተወሰደም በሚል የህወሓት አመራር ጥርጣሬ እንዲገባና እምነት እንዲያጣ ለማድረግ የሚከተሉት የትግል ስልት ነው።እነዚህ ሃይሎች ህወሓት ጠንካራ አመራር እንዲኖራት አሳስቧቸው አይደለም። በህወሓት«ተሃድሶ አልተካሄደም፣እርምጃ አልተወሰደም»ብለው የሚገልፁት ህዝቡ አመራሩን በጥርጣሬ እንዲያየውና የህወሓት አመራር እንዲመታ ነው።የትግራይ ህዝብና የህወሓት ትግል ለመምታት ኢላማ ያደረገ መጥፎ አካሄድ ነው።ተልእኳቸው ህወሓትን ማፍረስ ነው።እነዚህ ሃይሎች ፀረ ወያነና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ናቸው።ስለዚህ መላው አባላችን፣መላው ህዝብ ከተሃድሶ መድረኩ ጎን ለጎን በእነዚህ ሃይሎች ላይ የሚያደርገውን ትግል በንቃት አጠናክሮ ሊቀጠል ይገባል የሚል አስተያየት አለ።

**ወልቃይትና የህወሓት አቋም**

ማንነት በሚመለከት መጀመሪያ አንድ ነገር ልበል።ወልቃይት በትግራይ የሚገኝ ህዝብና ወረዳ ስለሆነ ከሁሉም በፊት የማንነት ጥያቄ ስጋታችን አይደለም።ይህ ስጋት የሚሆንብን ህዝብና ድርጅት አይደለንም።ምክንያቱም ትናንት ህወሓት እና የትግራይ ህዝብ ህዝቦች በማንነታቸው እንዲኮሩ መስዋእትነት የከፈልን ስለሆን ነው።ስለዚህ እኛ የማንነት ጥያቄ የሚያሰጋንና

የሚያስጨንቀን አይደለንም።በህገ መንግስቱ የተደነገገው ማንነትን የማስከበር መብት የከፈልነው መስዋእትነት ውጤት ነው።

ነገር ግን በእውነት የማንነት ጥያቄ የሚመለከት በወልቃይት ህዝብ አለን?ማን ነው የማንነት ጥያቄ አንስቶ እየተንቀሳቀሰ ያለው፣ይህ ሃይል ማን ነው?ብሎ ማየት ተገቢ ይመስለኛል። የወልቃይት ህዝብ መቼ?በማን?ለምንድን? ነው ከትግራይ አስተዳደር ወጥቶ በጎንደር ግዛት ውስጥ የሆነው?የሚለው ለቀባሪ መርዶ መንገር ነው የሚመስለኝ።

የወልቃይት ህዝብ ማንነቱን ስላጣ፣የደረሰበት አድልዎ፣መደባዊና ብሄራዊ ጭቆና፣ትግራዋይ ማንነቱ የማጥፋት በደል ለመታገል ከህወሓት ጎን ተሰልፎ ታግሏል።ህወሓት (1971ዓ.ም አካባቢ )በወልቃይት እንቅስቃሴ ስትጀምር ደርግ፣ኢህአፓ፣አዴዩ...በነበሩበት ወቅት የወልቃይት ህዝብ ትክክልኛ ማንነቱ የምታረጋግጠለት፣የበደሉን ሸክም የምታራግፍለት፣መርታ ለድል ወደምታበቃው ህወሓት ያለማመንታት ጎርፏል።ማንነቱን ለማስከበር ታግሎ ደሙን አፍስሷል። መስዋእትነት ከፍሏል።ትግራዋይ ማንነቱ ለማስከበር በደሙ የታገለና በዚህም የሚኮራ ህዝብ ነው።

የወልቃይት ህዝብ ታግሎ በተወሰዋበት አላማ እና በህገ መንግስቱ መሰረትም የማንነቱ ጉዳይ ምላሽ ያገኘ ነው።ይህ ህዝቡ ራሱ ያውቀዋል።አሁን ደርሶ የማንነት ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም። አላነሳምም።ትናንት ለማንነቱ ደሙን አፍስሶ ማንነቱን ያረጋገጠ ህዝብ የማንነት ጥያቄ የሚያነሳበት ምክንያት ፈፅሞ የለም።

ማን ነው፣ለምንድንነው፣ ታድያ ጥያቄ እያነሳ ያለው?በኢትዮጵያ እና በትግራይ ህዝብ ግብዓተ መሬታቸው የተፈፀመው የትምክህት ሃይሎች ጥገኛ አመለካከታቸውና አላማቸው ለማሳካት የያዙት ፀረ ህዝብ፣ፀረ ልማትና ፀረ ሃገር አቋም ነው።ይህ ሃይል እኔ «ፀረ ልማትና ዴሞክራሲ ነኝ »ብሎ አይቀርብም።ይህን አቋሙን በግልፅ ቢያራምድ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አያገኝም። ስለዚህ ዋና ስልቱ ብሄራዊ መልክና ፍላጎት በሽፋንነት እየያዙ አላማን ለማስፈፀም የሚደረግ ጥረትና ተንኮል ነው።እነዚህ ጥገኛ ሃይሎች በማንነት ሽፋን የትምክህት አመለካከትን በስፋት

በማንፀባረቅ የሰው ልጅ በፖለቲካ አሰላለፉና አቋሙ ሳይሆን በዘር በመለየት በተለይ አንድ ዘር በሌላው ዘር ላይ ጥርጣሬና የተሳሳተ አመለካከት እንዲፈጠር የማድረግ አላማቸው ለማሳካት የሸረቡት ሴራ ነው።

ስለዚህ ይህ ጥያቄ የማን ነው?ከተባለ በጠባብነት መልኩ የትምክህት ሃይሎችና ጥገኞች የተወሰኑት ከሃገር ውስጥ የተወሰኑት ደግሞ ከሃገር ውስጥ ሆነው፣በብአዴን ውስጥም ይህን የጥገኛ ትምክህት አመለካከት የሚያስተናግድና ከዚህ ዓይነት የጥገኝነትና የመበስበስ ጫፍ ጋር የተሳሰሩ፣የፈረሰው የግዛት አንድነት ለመመለስ በማንነት ሽፋን የሚደረግ ፀረ ወያነ እንቅስቃሴ ነው።በማንነት ሽፋን የሚነሳው ጥያቄ የወልቃይት ህዝብ ጥያቄ አይደለም።የብአዴን ጥያቄም አይደለም።የአማራ ህዝብ ጥያቄም አይደለም።ሙሉ ለሙሉ የጥገኞችና የትምክህተኞች ነው። የወልቃይን የማንነት ጉዳይ የሚያነሱት ትናንት የአሸነፍናቸው ቅሬቶች ነው።በማንነት ሽፋን ወደ ቀደመው ስርዓት ለመመለስ የሚደረግ ሙከራ ነው።ስለሆነም ህወሓት ይህንን በፅናት ይታገለዋል።ሴራው የትግራይ ህዝበን የመበተን ስለሆነ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ በሙሉ አቅማቸው የሚታገሉት ፀረ ወያነ እንቅስቃሴ ነው።

ትግሉ የሚጀመረው ከራስ ነው።በውስጣችን ያሉ ብልሽቶች መጀመሪያ ማስወገድ አለብን። ጠባብነት ይሁን ፀረ ዴሞክራሲያዊነትን መታገል መጀመር አለብን።የራሳችንን ጉድለት ከመታገል ተነስተን በኢህአዴግ ውስጥ በአቋም ላይ የተመሰረተ ትግል፣በድርጅቶች መካከልም በአቋም ላይ የተመሰረተ ትግል እንዲኖር እናድርግ።ከዚህ አልፎ ግን የትምክህት አመለካከት በዋናነት መታገል ያለበት ብአዴን ነው።በቁርጠኝነትም መታገል ጀምሯል።እኛ ከትግል ወንድማችን ከሆነው ብአዴንና የአማራ ህዝብ ጋር ሆነን እንታገላለን።በዚህ ተሃድሶም በይፋ ተጀምሯል።

**የግጭ ጉዳይ**

በመጀመሪያ የግጭ ጉዳይ ከወልቃይት ጋር አይገናኝም።ትምክህተኞች ግን ሆነ ብለው ከአለፈው ጋር እያዛመዱ ለጥያቄያቸው ማባባሻና መቀስቀሻ ለመጠቀም ሳይለያዩ ነው የሚያራግቡት።

የግጮ ጉዳይ ግን በትግራይ ፀገዴና በአማራ ጠገዴ መካከል ያለ የወሰን ማካለል ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ በአንድ ምሽግ ላይ በወደቁት ብአዴንና ህወሓት፤የአማራ እና የትግራይ ህዝብ መካከል ትልቅ ጉዳይ ይሆናል የሚል ግምት ስላልነበረንና በውስጣችኝ እያደገ ከመጣው ብልሽት፣በተለይ ደግሞ ጥገኛና ትምክህተኛ ሃይሎች ከማንነት በተጨማሪ ሽፋን እንዲሆናቸው ስለሰሩበትና ስላራገቡት ያለመልኩ መልክ እየያዘ መጣ።ይህ በወቅቱ መፈታት የነበረበት ነው ብሎ ህወሓት ገምግሟል።አሁንም በፍጥነት መፍትሄ ማግኘት እንዳለበት መግባበት ላይ ተደርሷል።በአጭር ግዜ እንዲፈታ እቅድ ተይዞለታል።ሁለቱም ድርጅቶችም በመግባባት ይፈፅሙታል የሚል እምነት ነው ያለኝ።

**የህወሓትና ብአዴን ታሪካዊ ትስስር**

በመጀመሪያ ደረጃ ብአዴን እንደ ድርጅት አብዮታዊ ዴሞክራት ነው የሚለው ሊሰመርበት ይገባል።የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ይዞ አሁንም ትግል ላይ ያለ ድርጅት ነው የሚል እምነት አለኝ።የህወሓትና የብኣዴን ትስስር በተመለከተ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመርና በአንድ ፕሮግራም የምንታገል የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ነን።በኢህአዴግ ደረጃም ቢሆን እንደዛው ነው፣በአንድ መስመርና በአንድ አላማ የምንታገል ነን።የዚህ መሰረቱ ትናንት በአንድ ምሽግ ውስጥ የወደቅነበትና ደም ያፈሰስንበት ትግል ነው ።ስለሆነም ብአዴን አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ይዞ ወደፊት የሚገሰግስ ድርጅት ነው።የዚህ አንድ በቂ መገለጫ የሚሆነው አሁን እያካሄድን በአለነው ተሃድሶ በድርጅቱ ውስጥ ያቆጠቆጠው አደገኛ የትምክህት አመለካከትና ተግባር እንደ ድርጅት በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር በፅናት መታገል ጀምሯል።እየታገለውም እየሄደ ነው።በመስመሩ መመከት ጀምሯል።

የድክመቶችና ብልሽቶች ጉዳይ በይዘታቸው ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር በሚኖረው አደጋ በሁሉም ብሄራዊ ድርጅቶች ህወሓትን ጨምሮ ያጋጠመው የመበስበስና የጥገኛ አመለካከት በይዘቱ፣በአደጋውና በፖለቲካዊ ትርጉሙ ህወሓት ላይ ይሁን ብአዴን ላይ ያጋጠመ ችግር ተመሳሳይ ነው።የብአዴን ልዩ የሚያደርገው የትምክህት አመለካከት ጫፍ ወጥቶ በአንድ

ምሽግ ላይ የተሰው ህዝቦችን ከአመለከካት አልፎ በተለይ በትግራይ ብሄር ላይ ወንጀል ወደ መፈፀም የተሸጋገረ አመለካከት መሆኑ ብቻ ነው።ከፍተኛው አመራር ችግሩ በተገለፀበት፣ በታየበት መጠንና በአስከተለው አደጋ እያንዳንዱ ሂስና ግለ ሂስ ለማድረግ ተሞክሯል የሚል እምነት አለኝ።በግምገማ፣በሂስና ግለሂስ የተኬደው ርቀት ቀላል ነው የሚል ግምት የለኝም። በህወሓት ከተካሄደው ግምገማ ለይቼ አላየውም።በአግባቡ እንደተገመገመ ነው የማውቀው።

በብአዴን የተካሄደው ትግልና የተጠያቂነት ሁኔታ በቂ ነውን ብሎ መጠየቅ በድርጅቱ በአጠቃላይም በኢህአዴግ እንዲሁም በቀጣይ ብአዴን ለሚያካሂደው ትግል የሚጠቅም ስለሆነ ጥያቄው መነሳቱ ችግር የለውም።እስካሁን በተካሄዱት የመጀመሪያ ምእራፍ መድረክ ብአዴን በታዩት ችግሮችና ብልሽቶች ምንጭ የሆነው አመለካከት እንደ ሁሉም ድርጅቶች ትግሉን ለኩሷል የሚል አስተያየት አለኝ።ፀረ ትምክህት ትግሉ አጠናክሮ እንደሚቀጥለም ምንም ጥርጥር የለኝም።

**የመልካም አስተደዳር ጉዳይ በትግራይ**

በተሃድሶው ቁልፍ የመገማገሚያና የሂስ ግለሂስ ጉዳይ አድርገን ከወሰድመው አንዱ የመልካም አስተደዳር፣የህዝባዊነትና የውግንና መሸርሸር ይገኙበታል።ሁሉም ከላይ እስከ ታች በዚህ መንገድ ተገምግሟል።ሲቪል ሰርቪሱም ተገምግሟል።መልካም አስተዳደር የማስፈን አመለከካት ለማረጋጋጥ በሚደረገው ትግል ይህ ተሃድሶ መሰረት ይሆናል የሚል እምነት አለ።እያንዳንዱ አመራርና ባለሙያ በተገመገመው፣ግለሂስ በአደረገው፣መጠየቅ አለብኝ ብሎ ንስሃ ከገባለት ጉድለቱ አርሞ መልካም አስተዳደር ለማስፈን በቂ ትግል ያደርጋል የሚል እምነት አለ። ያካሄደነው ተሃድሶ መልካም አስተዳደር ለማስፈን ጥሩ መሰረት ሆና ያገለግላል ብዬ አምናለሁ። በመልካም አስተደዳር ጉዳይ ሙሉ ስምምነትና መግባባት መኖር አለበት ብዬ አምናለሁ።ሂደት ነው።አሰራር ነው።አሰራር ስለሆነ ብቻ ሳይሆንም ከፖለቲካል ኢኮኖሚ ለውጥ ጋር የተሳሰረ ነው። በግምግማና በሂስ የሚያለቅ ሳይሆን በቀጣይነት በማያቋረጥ ህዝባዊ ትግልና በተቋማት ግንባታ ተደርጎ መወሰድ አለበት።የማያቋርጥና ሰፊ የህዝብ ተሳትፎና ትግል የሚጠይቅ ነው።

ሁላችንም መልካም አስተዳደር ለማስፈን ወደሚደረገው ትግል ስንመጣ እንደልማዳችን ድርጅታችን ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ግንባር ላይ ተሰልፈን በሚናደርገው ትግል የማንሻገርው ጉድለትና ችግር የለም።ስለዚህ ሁሉም የምናደርገው ትግል በተቀናጀ መንገድ መሆን አለበት።